ቅንጅት የዓለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ኮሚቴ
**Kinijit International Leadership**
kinijitinternational.org

ሚያዝያ 1 ቀን፣ 1999 ዓ.ም

# ድርጅታዊ ውሳኔ

## ለሁሉም የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች

ቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር በመሪዎቻችን እውቅና ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ፤ የተጣለበትን ግዴታና ሃላፊነት በትጋት ሲወጣ መቆየቱ የሚታወስ ነው። ሆኖም ራሳቸውን ከዚህ አመራር አካል ያገለሉ ግለሰቦችና ጥቂት ተከታዮቻቸው በተደጋጋሚ አፍራሽ ተግባራትን ሲፈጽሙበት ቆይተዋል። ለዚህም ተግባራቸው ፤ በቅንጅት ስም በከፈቱት ድረ-ገጽ እና ሬዲዮኖች ጭምር በመጠቀም የህዝቡን የትግል መንፈስ ለመበረዝ፤ ጥረት ቢያደርጉም ሊሳካላቸው አልቻለም።

ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ጉዳዮችን በሰከነ መንፈስ በማጤንና፤ ተከባብሮ መስራትን መሰረት በማድረግ እስካሁን ለተፈጸሙበት የስም ማጥፋት ዘመቻ በግለሰብም ሆነ በቡድን ምንም አይነት ምላሽ አልሰጠም። ለወደፊትም ለእንዲህ አይነቶቹ ተራ አሉባልታዎች ምላሽ በመስጠት ጊዜ የማጥፋት ፍላጎት የለውም። ይልቁንም እነዚህን የመሳሰሉ አስከፊ እኩይ ተግባራት እየተፈጸሙበትም እንኳ፣ ይህ ያመራር አካል ሰላማዊውን ትግል በአገር ውስጥና በውጭ አገር አጠናክሮ ህዝባችንን ለመታደግና መሪዎቻችንን ለማስፈታት፣ ደጋፊዎቻችንን ለማጠናከርና ጠላቶቻችንን ለማሳፈር፣ ያለአንዳች ቅድመ-ሁኔታ በመወያየት የእርቀ ሰላም እንዲወርድ አስታራቂዎችና ሽማግሌዎች ያቀረቡትን ጥሪዎች አስተናግዶአል።

ቀደም ሲል ፍጹም ህገወጥ በሆነ መንገድ ሲሶ ሚሊዮን ዶላር በማሸሽ፣ ድርጅቱንና የመሪዎቹን ትእዛዝ ክደው፣ ራሳቸውን ከቅንጅት አለማቀፍ አመራር ማግለላቸውን ስላወጁ ገንዘቡን ካልመለሱ አንደራደርም ያልነውን ቃለ ውሳኔ አንስተን በዋሽንግተን አካባቢ በሚኖሩ ሽማግሌዎች አማካኝነት ለመደራደር ብንጀምርም በነሻለቃ ዮሴፍ እምቢተኝነት ከሽፏል። ቀጥሎም የዛሬ ሁለት ወር አካባቢ የመጡት የቅንጅት አባላት ይህንን ማስማማት ቀጥለው ነበር። በበኩላቸዉ ባደረጉት ጥረት እራሱን ከአለማቀፍ አመራር ያገለለው ቡድን ለማሳሳቻ ከሚሰነዝሯቸው ጉዳዮች በተመለከተ፤

1. ቅንጅት አለማቀፍ አመራር የታሰሩ መሪዎች የቅንጅትን የፖለቲካ ስራ እንዲሰራ በውክልና የመደቡት አካል መሆኑን፣
2. በመደጋገም የሚያነሱአቸውና ስማቸውን የሚያጠፉአቸው ሁለት የአመራር አባላት በመሪዎቹ የታመኑና ለትግሉም አስተዋጻኦ ያደረጉና አሁንም በማድረግ ላይ ያሉ መሆናቸውን፡ ለነሻልቃ ዮሴፍ ቡድን ከመግለጻቸውም በላይ ለድጋፍ ድርጅት አባላት በተለያየ መድረክ አስረድተዋል።

በኛ በኩል እነሻለቃ ዮሴፍ የሚያደርሱብንን ስድብና ዘለፋ በድርጅቱ ላይም ያደረሱትን ጉዳት፣ ሰላምን ለመፍጠር ብቻ በማሰብ ችላ በማለት፣ ያለቅድመ ሁኔታ ለድርድር ስንቀርብ በነሱ በኩል ግን አስር ያህል ቅድመ ሁኔታ በመዘርዘር በተጨማሪም በወያኔ ተከሰዉ በሚፈለጉ ሁለት የአመራር አባላት ካልተወገዱልን እርቅ አንሻም በማለታቸው የሰላሙ ሙከራ መክሸፉን ሁለቱ አስታራቂዎች ወደ አዲስ አበባ ባስተላለፉት መልክት አስረድተዋል።

በዚህ በቀውጢ ቀን በብርቅየ መሪዎቻችን ላይ የሞትና የድሜ ልክ እስራት ቅጣት እያንዣበበባቸው መሆኑን በመረዳት ያለንን አቅም አስተባብረን የዜግነት ግዴታችንን ለመወጣት የተቻለንን ሁሉ ማድረግ እንዳለብን እናምናለን።

ስለዚህ ቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር የተጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት በተሰጠው ውክልና መሰረት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ውሳኔዎችን በመስጠት ሰራውን መቀጠል ምንም አማራጭ የሌለዉ ጉዳይ ሆኖ አግኝቶታል። ለዚህም እንዲረዳው በሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት አስቸኳይ ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

1ኛ- የትኩረቱን አቅጣጫ የበለጠ ወደ ትግሉ በመመለስ በአገር ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ያጠናክራል፤ ለዚህም አስፈላጊ የሆነውን የፖለቲካ አመራር ይሰጣል።

2ኛ- በውጭ አገር የሚገኙ ደጋፊዎችን የበለጠ በማበረታታት፤ የአገር ቤቱ እንቅስቃሴ አስፈላጊውን የፋይናንስና የዲፕሎማሲ ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል።

3ኛ- ከቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ራሳቸውን ባገለሉ ግለሰቦች ምትክ ለትግሉ የሚጠቅሙ ሌሎች አመራሮችን አስፈላጊውን ምክክር በማድረግ ይተካል እንዲሁም በመላው አለም ከሚገኙ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ጋር ያለውን ትሥሥር ያጠናክራል።

ስለሆነም ከላይ የተገለጹትንና በአጭር ጊዜ ልናከናውን ላቀድናቸው ተግባራት የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን እንዲቀጥሉ እንጠይቃለን።

ሰላማዊ ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥላል

የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር

**Kinijit International Political Leadership Secretariat, P.O.Box 14701 Silver Spring MD, 20911 USA**
**Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974 www.kinijitethiopia.org**